# መጽሐፈ ነህምያ(5)

## ጥናት አንድ (ነህምያ 1፥1-11)

የጥናቱ ዓላማ፡- በእግዚ አብሄር ቤት ውስጥ የችግር መንስሄዎች ሳይሆን ለሚፈጠሩት ችግሮች በተግባራችንና በጸሎታችን መፍትሄ የምንሆን ሰዎች እንድንሆን ለማስገንዘብ።

የጥናት መክፈቻ፡- በሃገራችን አንድ አስደከፊ ነገር እንደ ጦርነት ወይም ረሃብ መነሳቱን ስትሰማ የሚሰማህን ስሜት ግለጽ።

1. ነህምያ ምዕራፍ 1 ይነበብ። በቁጥር 1-3 ባለው ክፍል የሚደረገው ውይይት ምንን በተመለከተ ነው?
2. የሃናኒን ሪፖርት በሰማ ጊዜ ነህምያ ያደረጋቸው አራት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. ነህምያ ከቁጥር 5-11 ባለው በጸሎቱ ላይ ያተኮረባቸውን ነገሮች ዘርዝር። የዚህ ሰው የጸሎት አይነት ጋራ ራስህን ጸሎት ስታነጻጽር ምን ይመስላል?
4. ነህምያ እግዚአብሄር ጸሎቱን እንደሰማውና እንደሚመልስለት ማመኑን የሚያሳይህ ክፍል የትኛው ነው?
5. ነህምያ በጾመና በጸለየ መጠን ልቡ እየሞላ ሲሄድ ይታያል። ይህ በመሆኑ ለሥራው ራሱን ለመስጠት እንዴት የረዳው ይመስልሃል?
6. በዚህ ክፍል ነህምያ ከወሰደው እርምጃና ከጸሎቱ ስለ እርሱ ባህርይ ምን መማር እንችላለን?
7. ባለንበት ቤተ ክርስትያን የእግዚአብሄር ስራ ሲበላሽ ወይም በመፍረስ ላይ መሆኑን ስታይ ወይም ስትሰማ ልትወስድ የሚገባህ እርምጃ በትምህርቱ መሰረት ምን ይመስልሃል?
8. ዛሬ በተማርከው አንጻር ስታየው የእግዚአብሄር ቤት ፈርሶ ስታይ ያንተ ሃላፊነት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
9. በቀሪው ዘመንህ ጌታ ለቤቱ የችግር መፍትሄ እንጂ ችግር ምንጭ እንዳትሆን ቁርጠኛ ውሳኔን አድርግ።

# ጥናት ሁለት (ነህምያ 2፥1-20)

የጥናቱ ዓላማ፡- እንደ ነህምያ እኛም የእግዚአብሄርን ሥራ ስንሰራ ጸሎትን፥ ማቀድን፥ ድፍረትንና የመንፈስ ጥንካሬን መያዝ እንደሚያስፈልግን እንድንረዳ ለማድረግ።

የጥናት መክፈቻ፡- ለምን ይመስልሃል እኛ ክርስትያኖች ለእግዚአብሄር ትልቅን ሥራ ለመስራት የማንደፍረው?(ሥጦታ እንደሌለን ማሰብ፥ስንፍና፥ምሪት ማጣት...ወዘተ)

1. ነህምያ ምዕራፍ 2 በህብረት ይነበብ። ቁጥር 1-9 ስናነብ ስለነህምያ ዕቅድና ዝግጅት ያስተዋልካቸውን ነገሮች ዘርዝር።
2. ነህምያ በምዕራፍ 1 በሚፀልየው ጸሎትና በምዕራፍ 2፥4 በሚፀልየው ፀሎት መሃል ያለው ልዩነት ምንድነው?
3. እግዚአብሄርን ለማያውቅ ንጉሥ ነህምያ ለመናገር ድፍረትን ከየት አገኘ? ይንን በማድረጉ ሊያስከትልበት የሚችለውን ችግር ተርድቷል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
4. ሥራውን ከመጀመሩ አስቀድሞ ነህምያ የስራውን ውስብስብነት ለመገንዘብ የወሰደውን እርምጃ በቁ 11-16 እናያለን። ከዚህ ድርጊቱ እኛ ምን መማር እንችላለን?
5. ለምንድነው ነህምያ በቁጥር 17-20 ላይ የዚህ ዓይነት ልበሙሉነትን በተሞላው መንፈስ የሚናገረው?
6. ለተጠራህበት የእግዚአብሄር ሥራ ሊገጥምህ ስለሚችለው ነገርና እንዴትስ ለዚያ መዘጋጀት እንዳለብህ ከነህምያ ምን ትማራለህ?
7. በምዕራፍ 1 የነህምያን ጸሎት ከምዕራፍ 2 ደግሞ የነህምያን ተግባር/ሥራ ተመልክተናል። ሁለቱን ምዕራፎች በማየት የእግዚአብሄርን ሥራ በተመለከተ ጸሎትና ተግባር በእግዚአብሄር ስራ ውስጥ ስላላቸው ቦታ ምን እንማራለን?
8. የእግዚአብሄር ስራ ጸሎትን፥ ማቀድን፥ ድፍረትንና ጥንካሬን ሁሉ ስለሚያካትት አንደኛውን ብቻ ይዘህ ሌላውን እንዳትጥል ጥንቃቄ አድርግ።

# ጥናት ሶስት (ነህምያ 3፥1-32)

የጥናቱ ዓላማ፡- እግዚአብሄር የሚሰጥንን ራዕይ በራሳችን ብቻ መታገል እንደሌለብንና ብዙዎችን በማሳተፍ ሸክማችን እንደሚቀል እንዲሁም ሥራው ደግሞ እንደሚገባው እንዲፋጠን ለማድረግ የሚበጅ መሆኑን ለማየት።

የጥናት መክፈቻ፡- በጌታ አገልግሎት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መሰጠት ከማይችሉ ሰዎች ጋራ አገልግለህ ታውቃለህ? ለምን ይመስልሃል ሰዎች ብዙ ጊዜ መሰጠት የማይፈልጉት?

1. ምዕራፍ 3 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ምዕራፍ የኢየሩሳሌምን ቅጥርና በሮች ለመጠገን የተሳተፉትን ሰዎች ጥቂቶችን ዘርዝር።
2. ይህንን ምዕራፍ ስትመለከት ሰዎቹ በሥራው ላይ እንዲሳተፉ የገፋፋቸው ዋናው ምክንያት ምንድነው ትላለህ?
3. የዚህ ሁሉ ሰው በሥራው ላይ መሳተፍ ለነህምያ ራዕይ ምን ያህል አስተዋጽዖ ነበረው ማለት ያስችለናል?
4. የስራ ክፍፍልን በተመለከተ ከዚህ ምዕራፍ ምን ዓይነት መመሪያ ማውጣት እንችላለን?
5. በቤተክርስትያናችን ውስጥና እንዲሁም በሌሎች አብያተ ክርስትያናት ይህ መመሪያ ማለትም የብዙዎች በሥራው ላይ መሳተፍ ምን ያህል ተግባራዊነቱን ታያለህ? ይህ እንዲሆን እያንዳንዳችን ምን ሃላፊነት ይኖርብናል ትላለህ?
6. ፕሮጀክቱን ጀምሮ ለመፈጸም የተጠቀመባቸው ነገሮች 1)ጸሎት 2)ራዕይ 3)ለስራው ዕቅድ መንደፍ 4)ሰዎችን ማስተባበርና 5)ሥራውን ማከናወን ናቸው። ይህንን አሰራር መረዳት ለተሰማራንበት/ለምንሰማራበት ሰራ ምን ያህል ጠቃሚነት እንዳለው ትገምታለህ?
7. ሥራውን ለማከናወን በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ አስትዋጽዖ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ለምንድነው? በቤተክርስትያን ውስጥስ የአንተ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ ምን ያህል ገብቶሃል? የእግዚአብሄር ቃል ይህንን ሃሳብ በመደገፍ የሚናገረው አንድ ክፍል ተናገር።
8. አንተስ የተሰጠህን ራዕይ ለመወጣት ምን ያህል በጎንህ ያሉትን ወገኖችህን ታሰማራለህ? በህብረት ውስጥ በረከት እንዳለም አትዘንጋ።

# ጥናት አራት (ነህምያ 4፥1-23)

የጥናቱ ዓላማ፡- የእግዚአብሄርን ሥራ ለመሥራት ስንነሳ ሰይጣን ዝምብሎ እንደማያየንና እኛም ተቃውሞ ሊመጣብን እንደሚችል በመገንዘብ በንቃት የሥራውን ባለቤት በመተማመን ተስፋ ሳንቆርጥ ወደፊት መግፋት እንደሚኖርብን ለማየት።
የጥናት መክፈቻ፡- በአገልግትህ ጠላት ውግያ አስነስቶ አይተህ ታውቃለህ? ውጤቱስ ምን እንደነበረ ታስታውሳለህ?

1. ነህምያ ምዕራፍ 4 በህብረት ይነበብ። በም6፥1-6 መሰረት የጦብያና የሰንባላጥን ስሜት እንዲሁም በሥራው ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል አስረዳ።
2. ነህምያ ለእነዚህ ለመጡበት ማስፈራራቶችና ተቃውሞዎች በምን ዓይነት እንደመለሳቸው ተናገር (ቁ 1-6)።
3. እንደ ጦብያና ሰንባላጥ ማስፈራራት ሕዝቡ ሥራውን አቁሞ መበታተን ነበረበት። ለምንድነው ሕዝቡ በቆራጥነት ሥራውን መሥራት የቻለው?
4. ቅጥሩ እንዳይጠገን ለመከልከል የመጣውን ጠላት ያስነሳውን አዲሱን ማስፈራሪያ በቁጥር 7-12 በማየት በራስህ ቃላት ግለጽ።
5. ጦብያና ሰንባላጥ ከሚያስፈራሩት ሌላ ከውስጥም የሚረዳቸው እንዳለ በቁ 10 እና 12 ላይ ይታያል። እነዚህ ምን እንደሆኑ ግለጽ።
6. ቁጥር 13-20 በማንበብ ለእነዚህ አዲስ ለመጡት ማስፈራሪያዎች ነህምያ በምን ዓይነት ነበረ መልስ የሰጠው?
7. ነህምያ ለሥራው መከናወን የሚተማመነው በምንድነው? (ቁጥር 9, 14, 20)
8. ሥራው እንዳይሰራ ለሚመጣው ተቃውሞ ነህምያ ከወሰዳቸው እርምጃዎች ምን እንማራለን?
9. ዛሬ የተማርከው እውነት ወደፊት የሚገጥምህን የሰይጣን ተቃውሞ በተለየ መንገድ ማስተናገድ እንድትችል እንዴት እንድሚረዳህ ለወገኖች አካፍል።

# ጥናት አምስት (ነህምያ 5፥1-19)

**የጥናቱ ዓላማ፡-** በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ተቀምጠን የመንግሥቱን ሥራ መስራት ሲገባን ለሚሰሩት እንቅፋትና ተስፋ የመቁረጣቸው ምክንያት እንዳንሆን ለመማር፡፡

**የጥናት መክፈቻ፡-** ሰዎች አብረውህ በአንድ ራዕይ ሥር እየሰራችሁ በመሃል ለራሳቸው የጥቅም ማፍሪያና ለግል ጥቅማቸው ሁኔታውን ሲጠቀሙበት ብታይ ምን ይሰማሃል?

1. ነህምያ 5፥1-19 በህብረት ይነበብ። በቁጥር 1-5 ውስጥ የሚገኙ ሶስት ከውስጥ የሚነሱ ተቃውሞዎችን ዘርዝር።
2. እነዚህን ችግሮች መንስሄዎች እነማን ናቸው? ችግር የደረሰባቸውስ እነማን ነበሩት?
3. በቁጥር 7-12 ላይ የታላላቆችንና የሹማምንቶችን በቁጥር 14-18 ደግሞ የነህምያን አኗኗር እናነባለን። ለምንድነው ነህምያ የዚህ አይነቱን ኑሮ የመረጠው?
4. ከውስጥ ለተነሱበት ችግሮች ነህምያ የሰጣቸው መፍትሄዎች ምን ምን እንደሆኑ አስረዳ፡፡
5. የታላላቆችና የሹማምንቱ ምግባር አሁን ባለንበት ዘመን ሲንጸባረቅ ታያለህ ወይ? የነህምያን ፈለግ የሚከተሉስ ሰዎች ታያለህ ወይ?
6. ነህምያ ከውስጥ ለተነሳው ችግር ተካፋይ ሳይሆን ለችግሩ መልስ ለመሆን የበቃበትው በምን ምክንያት ነው ብለህ ትገምታለህ?
7. በዛሬ ጥናት መሰረት የቤተክርስትያን መሪዎች ለምንድነው ከውጭም ከውስጥም ሊነሱ ለሚችሉ ችግሮች ራሳቸውን ማዘጋጀት የሚኖርባቸው?
8. በምዕ 4 ውስጥ ከውጭ ስለሚነሱ በምዕ 5 ደግሞ ከውስጥ ስለሚነሱ ችግሮች ተመልክተናል። የትኛው የበለጠ አስቸጋሪ ነው ብለህ ታምናለህ? ለምን?
9. አማኞችን ሲያፍረከርክ የሚገኘው ከውስጥ የሚነሳው ችግር በመሆኑ ችግር ፈጣሪ አለመሆን ብቻ ሳይሆን የችግሩ መፍትሄ አድርጎ እንዲጠቀምብህ ጌታን ለምን።

# ጥናት ስድስት (ነህምያ 6፥1-19)

የጥናቱ ዓላማ፡- ሰይጣን ሁልጊዜ በአንድ አይነት መንገድ ብቻ እንደማይመጣና በአንድ በኩል ስንዘጋበት ተስፋ ሳይቆርጥ ሌላ ወጥመድ እንደሚያበጅ በመረዳት ዘወትር ዝግጁ ሆነን ትጥቃችንን ሳንፈታ መቆም እንደሚኖርብን ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፡- የእግዚአብሄርን ሥራ እንዳትሰራ ለማስቆም ጠላት ያስፈራራህ ጊዜ አለ ወይ? የምታስታውሰውን ያህል ለወገኖች ለመግለጽ ሞክር።

1. ነህምያ 6፥1-19 በህብረት ይነበብ። ባለፉት ምዕራፎች ውስጥ ጦብያና ስንበላጥ ሌሎችንም ጨምሮ ህዝቡ ቅጥሩን እንዳይሰሩ ለመከላከል ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች ይህ በምን ይለያል?
2. ነህምያ እንገናኝ ለሚለው ጥያቄአቸው የሰጠው ምላሽ ምን ነበረ? ከምላሹ ነህምያ ስለተሰማራበት ሥራ ስላለው አመለካከት ምን ይነግረናል? ከዚህ ምን እንማራለን?
3. ቁ4 ትን ስታነብ ስለ አይሁድ ጠላቶች ልንረዳ የምንችለው አንድ ትልቅ እውነት ምንድነው?
4. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚታዩትን የማስፈራራት ዘዴዎች በየተራ ዘርዝር።
5. የጠላቶቻቸው በተለያየ ዘዴ መጠቀምና እንዲሁም ሰልችተው አለመተዋቸው ለአንተ ህይወት ምን ትምህርት ይሆንሃል?
6. ቁጥር 17-19 ላይ የሚካሄደው ነገር ነህምያ ከጠላቱ ጋራ ለሚያደርገው ፍልሚያና የነበረውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ምን ያህል ተወሳሳቢ ያደረግበታል?
7. ይህ በቁጥር 17-19 የምናነበው ሁኔታ በእኛ አገልግሎትና በቤተ ክርስትያናችን ሊከሰት የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ተናገር።
8. ጠላትን የምትጠብቀው በየትኛው አቅጣጫ ነው? ባላሰብከው መንገድ መጥቶብህ ያውቃል ወይ? የጠላትህ መምጫው ብዙ ስለሆነ ሁልጊዜ ዝግጁ ልትሆን ያስፈልግሃል።

# ጥናት ሰባት (ነህምያ 8፥1-18)

የጥናቱ ዓላማ፡- በግለሰቦችም ሆነ በቤተ ክርስትያን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንዲነሳ ካስፈለገ የእግዚአብሄር ቃል ማዕከላዊውን ሥፍራ መያዝ እንዳለበት ለማሳየት።
የጥናት መክፈቻ፡- ክርስትያን ጭምት መሆን እንጂ መሳቅና መጫወት መንፈሳዊነቱን ይቀንሳል ስለሚለው አመለካከት ምን ሃሳብ አለህ?

1. ነህምያ 8፥1-18 በህብረት ይነበብ። በቁጥር 1 መሰረት ህዝቡ እንዲከናወን የፈለገው ነገር ምን ይመስላል? ይህንንስ በምን መንገድ ገለጸው?
2. ቁጥር 2-3 ስናነብ የእግዚአብሄርን ቃል ለመስማት ስለተሰበሰበው ህዝብ በተደጋጋሚ የሚነግረን ነገር ምንድነው?
3. በቁጥር 3-12 ውስጥ ለእግዚአብሄር ቃል ስላላቸው አክብሮት ከሚናገሩት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹን ዘርዝር።
4. ቁ 2, 3, 8 ላይ ስለማስተዋል ደጋግሞ ይጥቅሳል። በእግዚአብሄር ቃልና በማስተዋል መሃል ስላለው ግንኙነት ምን ትረዳለህ?
5. በቁጥር 9 ላይ ህዝቡ ለምን የሚያለቅሱ ይመስልሃል?
6. ቁጥር 11-12 ስትመለከት የእግዚአብሄር ቃል በህዝቡ ላይ ሊያመጣ ስለቻለው አዲስ ነገር ምን ትመለከታለህ?
7. በዚህ ምዕራፍ የሚታየው በእስራኤል ልጆች ያነበብነውን ሃሳብ በዘመናችን በምን መንገድ ልንለማመደው እንደምንችል ተናገር።
8. ቁ10-12 ላይ የእግዚአብሄር ቃል በሰሚዎቹ ህይወት ላይ ያስከተለውን ዓይነት ደስታን ሃሴት በህይወትህ ሲሆን ታያለህ ወይ? ለግልም ሆነ ለጋራ መነቃቃት ቃሉ ዋነኛ ነገር ስለሆነ ተጠቀምበት።

# ጥናት ስምንት (ነህምያ 9፥1-38)

የጥናቱ ዓላማ፡-የእግዚአብሄር ቃል እንደግለሰብም ሆነ እንደ ቤተ ክርስትያን መንፈሳዊ እንቅስቃሴን ሲያመጣ እንቅስቃሴው እንዲቀጥል ካስፈለገ ቃሉን በመታዘዝ እውነተኛና ከልብ የሆነ ንስሃ መግባት እንደሚያስፈልገን ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፡- እንደ ቤተ ክርስትያን የሃጥያት ንስሃ ሲገባ ገጥሞህ ያውቃል? ያን ጊዜ አንተ ምን ስሜት ተሰማህ?

1. ነህምያ ምዕ 9፥1-38 በህብረት ይነበብ። ቁጥር 1 የእስራኤል ልጆች ጾመውና ማቅ ለብሰው ንስሃ ሲገቡ ያሳየናል። ለዚህ ንስሃቸው የእግዚ አብሄር ቃል ምን ሥፍራ ነበረው ትላለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ 8፡18 ይነበብ።
2. በተለይ ቁ2 ትን ስንመለከት የአባቶቻቸውን ሃጥያት ሁሉ ሲናዘዙ ይታያል። የእነርሱን ሁሉ በደል የሚናዘዙበት ምን ምክንያት ታያለህ?
3. በምዕራፍ 9 ከምንመለከተው ሁኔታ በመነሳት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንዲቀጥል ካስፈለገ መደረግ የሚኖርበት ዋነኛ ነገር ምንድነው?
4. የእስራኤል ልጆች ስለገቡት የንስሃ ዓይነት ስትመለከት ምን ታስተውላለህ? ንስሐው ድፍን ያለ ነው ወይስ ቀጥተኛና ያልተደባበቀ ነው?
5. እነርሱ ከገቡት የንስሃ ዓይነት እንደግለሰብና እንደ ቤተ ክርስትያን ምን መማር እንችላለን ብለህ ታምናለህ?
6. በቁ 5-8 ስታነብ ምንም እንኳን የራሳቸውን ሃጥያት እና አለመታዘዝ ቢገነዘቡም ስለ እግዚአብሄር የነበራቸው አስተሳሰብ ምን ይመስል ነበረ?
7. በቁ 33 መሠረት ስለሐጥያታቸው ጣቶቻቸውን የሚጠቁሙት ወደ ማን ነው?
8. ስለሃጥያትህ ሙሉ ሃላፊነትን መውሰድ ምን ያህል ያስቸግርሃል? ንስሃህስ ምን ያህል ግልጽነት አለው? የሃጥያት ንስሃ ለመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ወሳኝነት እንዳለው አውቀህ ለሃጥያትህ ሰውን ምክንያት ማድረግ አቁምና ራስህ ሃላፊነቱን መውሰድ ተለማመድ።

# ጥናት ዘጠኝ (ነህምያ 10፥1-39)

የጥናቱ ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ቃል ሲነካንና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በህይወታችን ሲመጣ ለውሳኔና መሥዋዕትነት በመክፈል ለመኖር እንደሚያነሳሳን ለመመልከት።
የጥናት መክፈቻ፡- ቃል ኪዳን ገብተህ ቃልህን ለመጠበቅ የተቸገርክበት ወቅት አለ? ያኔ ምን እርምጃ ወሰድክ?

1. በ9፥38 ቃልኪዳን እንደገቡ አንብበናል። 10፥28-29 ላይ ቃልኪዳን የገቡት ሰዎች እነማን ናቸው?
2. ከቁ 30-39 በማንበብ ሰዎቹ በእግዚአብሄር ፊት ቃል የገቧቸውን ነገሮች ዘርዝር።
3. ከላይ የዘረዘርናቸው አብዛኛዎቹ ነገሮች መንፈሳዊ ሳይሆኑ ቁሳቁስን የተመለከቱ ናቸው። ለምን ይመስልሃል ይህ የሆኑበት ምክንያት?
4. በዚያን ጊዜ ከአህዛብ ጋራ ያለመጋባታቸው በጣም አስፈላጊ የነበረበት ምክንያት ለምንድነው?
5. ዛሬ በቤተክርስትያን ለእግዚአብሄር መስጠት አለብን ብለህ የምታምነው ቁሳዊ ነገሮችን ዘርዝር።
6. ቁጥር 30 በአንድነት ይነበብና ይህ እነርሱ የገቡት ቃል ኪዳን በእኛ ሕይወትስ በምን ዓይነት ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችላል ብለህ ታምናለህ?
7. ቁ 37-38 ባለው ክፍል ህዝቡ በሌዋውያን በኩል አስራታቸውን ለማምጣት ሲወስኑ ከሌዋውያኑ ስለሚጠበቀው ነገር ምን ሃሳብ እንደተሰነዘረ ተናገር።
8. ከዚህ ክፍል መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥህን ከማሞቅ አልፎ ማድረግ ስለሚገባህ ነገር ምን አስተማረህ? መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ልብንም ኪስንም ስለሚነካ አንተም በሁለቱም በኩል መነካትህን አረጋግጥ።

# ጥናት አስር (ነህምያ 11፥1-36)

የጥናቱ ዓላማ፦ ሰው ማናቸውንም የመኖሪያ ሥፍራ ቢመርጥ ከእግዚአብሄር መንግሥት ሥራ ነጻ ሊሆን እንደማይችል ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፦ የት እንደምትኖር ስትወስን የምታያቸው ነጥቦች ምን ምንድናቸው? ከነዚያ ነጥቦች ሌላ ተመልክቼ በሆነ ብለህ ተጸጽተህ ታውቃለህ?

1. ነህምያ ምዕ 11 በህብረት ይነበብ። በዚህ ምዕራፍ የምናያቸው አይሁዶች እንዴት ነበረ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን የወሰኑት?
2. ለምንድነው ህዝቡ በኢየሩሳሌም መኖር ያልፈለጉበት ምክንያት? (ቁ 2)
3. በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ሰዎች እንዲቀመጡ ያስፈለገበት ምክንያት ለምንድነው?
4. በምዕራፍ አስር ውስጥ በተመለከትነው መሰረት እዚህች ከተማ ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች በምን ዓይነት መንገድ ነው የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች የሚያገኙት?
5. በዚያን ሰዓት አንተ በእነሱ መሃል ብትኖርና በእርሻ ላይ ተሰማርተህ እህል ብታቀርብ ትመርጣለህ ወይስ ሌሎች ወደ እግዚአብሄር ቤት በሚያመጡት ሥጦታ መኖር ትመርጣለህ? ለምን?
6. በእኛ ዘመን ከእነሱ የተለየ የሆነው በምን በምን መንገዶች ነው? ክርስትያን በዘመናችን የት እንደሚኖር ሲወስን ምን ዓይነት መመሪያዎች መከተል የሚኖርበት ይመስልሃል? መልስህን በእግዚአብሄር ቃል መደገፍ ትችላለህ?
7. ይህንን ምዕራፍ ስታነብ የምትኖርበት ሥፍራና የጌታ አገልግሎት ምን ግንኙነት አለው ብለህ ታምናለህ? መልስህን አብራራ።
8. በኢየሩሳሌም ውስጥም ሆነ ከኢየሩሳሌም ውጭ ያሉት ሁሉ ለቤተመቅደሱ አገልግሎት ሃላፊነት እንደነበረባቸው ሁሉ አሁንም በዚህ ዘመን በማናቸውም ሥፍራ ብትኖር ለእግዚአብሄር መንግሥት አስተዋጽዖ የማድረግ ሃላፊነት እንዳለብህ አትዘንጋ።

# ጥናት አስራ አንድ (ነህምያ 12፥1-47)

የጥናቱ ዓላማ፡- የአገልግሎት ትንሽ እንደሌለው በማሳየት ሁሉም በተሰጠው ጸጋ እንዲሰማራ ለማበረታታት።

የጥናት መክፈቻ፡- ለምን ይመስልሃል በተለይም በእኛ ባህል አንዳንድ ሥራዎችን በአክብሮት ሌሎቹን ደግሞ በንቀት የምንመለከተው?

1. ነህምያ 12 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የብዙ ሰዎች ስም ተዘርዝሮ የሚገኘው ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ?
2. በቁጥር 24 ላይ ያሉትን ሰዎች ዓይነት ወይስ በቁ25 ላይ እንደተጠቀሱት ሰዎች የእቃቤት ጠባቂነትን አገልግሎት ትመርጣለህ? ለምን? ከሁለቱስ የትኛው ይበልጣል ትላለህ?
3. ከቁ27-43 ድረስ ባለው ክፍል ዋነኛውን ሥፍራ ይዘው የሚታዩት እነማን ናቸው?
4. በቁ 43 ላይ እግዚአብሄር ምን ሲሰራ ነው የምናየው?
5. የደስታው ተካፋይ የነበሩት እነማን ነበሩ? ለምንድነው እግዚአብሄር ይህንን የሚያህል ደስታ ማፍሰስ የፈቀደው?
6. በቁ45 ላይ የተጠቀሱት ሶስቱ የአገልግሎት ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር። ቁ25-26 ዘቦቹ አገለገሉ፥ ቁ42 መዘምራኑ ዘመሩ፥ ቁ45 ካህናትና ሌዋውያኑ የአምላካቸውን አገልግሎት ፈጸሙ። እዚህ ቦታ ሲያደርጉ የሚታየው ነገር ምንድነው?
7. በተራ ቁጥር 6 ከምንመለከተው ነገር ምን ትምህርት መቅሰም እንችላለን?
8. የጌታን ቤት ለመገንባት ሁሉም ዓይነት አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑን ምን ያህል ገብቶሃል? አንተ የገባህ ከሆን ለሌሎች ይህንን እውነት በማስተጋባት አበረታታ።

# ጥናት አስራ ሁለት (ነህምያ 13፥1-31)

የጥናቱ ዓላማ፡- መሪዎች በፍቅርና በትህትና ህዝቡን መምራት እንዳለባቸው ቢታወቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግን ልክ እንደ ነህምያ ትግሳጽንም ሆነ እርማታቸውን ሲያደርጉ በጸጋ የመቀበል ልብ እንዲኖረን ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፡- ቃል ኪዳን ገብተህ የገባኸውን ቃል ለመጠበቅ ተቸግረህ ታውቃለህ? በዚያን ጊዜ ምን አደረግህ?

1. ነህምያ 13፡1-31 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-3 ላይ የመጽሃፉ መነበብ የገለጠው ነገር ምን ነበረ?
2. ቁ4-7 ያለውን ክፍል ስናይ የነህምያ ወደ ንጉሥ አርጤክስስ መመለስ በእስራኤል ልጆች መንፈሳዊ ህይወት ላይ ያስከተለው ምን ሁኔታ እንደነበረ ተናገር።
3. በምዕራፍ 10 ውስጥ ያንን የመሰለ ቃልኪዳን የገቡ ሰዎች በዚህ በምዕራፍ 13 ውስጥ የሚታየውን ያህል ሁኔታ ውስጥ መግባት እንዴት ቻሉ ትላለህ?
4. ቁጥር 4-9, 28 ስናነብ ነህምያ ሰዎችን እንዲያውም የዋነኛውን ካህን ልጅ ሳይቀር እንዳባረረ እናያለን። ለምንድነው ይህንን ጭካኔ የመሰለ ድርጊት ለማድረግ የተገደደው?
5. ሁኔታዎችን ለማረም ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱን በቁ12-13 ላይ እናያለን። ይህ ድርጊት ምን ነበረ? ለሹመቱ ምክንያትና መሰረት የነበረው ነገር ምን ነበረ?
6. ነህምያ ተመልሶ መንፈሳዊ ሁኔታቸውን ሲመለከት የተሰማውን ሁኔታ ከገለጠባቸው መንገዶች አንዳንዶቹን ዘርዝር። ቁ8፥ 11፥ 25 28
7. ቁ25 ትን ስታነብ ምን ስለ ነህምያ አመራር ምን ትረዳለህ? ይህንን ዓይነት ድርጊት በዚህ ዘመን ያሉ መሪዎች በተግባር ላይ ሊያውሉ የሚችሉበት መንገድ አለ ብለህ ታምናለህ ወይ? አስረዳ።
8. የነህምያ ተመልሶ መምጣት በህዝቡ መንፈሳዊ ህይወት ምን ያህል ሚና ትጫውቷል ትላለህ?
9. በቁ25 ላይ ከስፈሩት ሰዎች አንዱ ብትሆን ምን ይሰማሃል? ስታለማ ለማመስገን ብቻ ሳይሆን መንገድ ስትለቅም ለማቅናት ስለሆነ ቤ/ክ ያለችው ልብህን ክፍት አድርገህ ተመላለስ።